Contact us: pr@ginbot7d.org

website: www.ginbot7d.org

# ለመገናኛ ብዙኃንና ለኢትዮጵውያን በሙሉ፤

# ከግንቦት 7 ዲሞክራቲክ የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ

## ጉዳዩ፡- አዲስ የፖለቲካ ድርጅታችንን ስለማሳወቅ

መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም.

መቼም ታሪክ ሲባል ለበጎ ትዝታ ወይም ለመጥፎ ትውስታ የዋለው ሁሉ ታሪክ ተሰኝቶ መዘከሩ አይቀርም፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት አራት አሰርተ ዓመታት በታሪኳ ካገጠሟት ፈተናዎች ሁሉ የነዚሁን ያህል አጋጥሟት አያውቅም ማለት ይቻላል፡፡ ምናልባትም ከጠላት ወረራና ከአንዳንድ የውስጥ ባላንጋራ በስተቀር፡፡ በፈጣሪዋም የተወደደችና የተመረጠች ትባል እንጂ ከአብራኳ የተከፈለነውና ከማኅጸንዋ የወጣነው ልጆቿ ግን ስማችንና ግብራችን አልገገናኝ ብሎ ሸክላ እንዳልጠገበ ሸክላ እያደር የሚፍረከረክ ሆኗል፡፡

ይህንን የአገር ችግርና የሕዝብ በደል ፍጻሜ ለማድረስ በተለያዩ ጊዜያት የተነሱ ወገኖች ቢኖሩም፤ አለመታደል ሆኖ እስካሁን የሰመረላቸው በተቃራኒው ቆመው አገርን ለሚንዱና ወገንን ለሚበድሉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ያቀደ የወጠነም ይሁን የተለመ ካሰበበት ለመድረስ የዓላማ ጽናትን፤ የሕዝብ መሠረትና የማሕበራዊ ፍትኅ ስፍነትነትን አካቶ መያዝ የግድ ይላል፡፡ ይሁን እንጂ የጥቂቶች አጥቂነት የብዙኃኑ ተጠቂነት ሰፍኖ እስከቀጠለ ድረስ፤ ከከፉ ድርና ማግ የተሰሩ፤ ማኅበራዊ ፍትኅን የሚዋጉ ኃይሎች እስካሉ ድረስ፤ በሕግ ስም ዲቃላ ሕግ ህግገው በእውነተኛው ሕግ ላይ የሚያላግጡ ኃይሎች እስቀጠሉ ድረስ፤ ትግሉ የወሰደውን ያህል ወስዶ ዳር መድረስ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ምሉ በኩለሄ የሆኑ መሪዎች በሻማ ይፈለጋሉ፡፡

መሪዎች ቅንነትን የተላበሱ፤ ፍትሃዊ፤  እራሳቸውን ዝቅ አድርገው የሌላውን ክብር የሚጠብቁ፤ ተጠያቂነት የሚሰማቸው፤ ግልጽ እና ታማኞች እንዲሁም የሚነሱ የሃሳብ ልዩነቶችን በቅን መንፈስ ማየት የሚችሉ ከየትኛውም ወገን ሳይወግኑ ለመመርመር ድፍረቱ ያላቸው፤ እውነተን ፊት ለፊት ለመጋፈጥ የማይፈሩ  መሆን ይጠበቅባቸዋል። መሪዎች  ሲሳሳቱ ለመታረም የተዘጋጁና ይቅርታ መጠየቅ ካለባቸው ጥፋታቸውን ፊት ለፊት ተጋፍጠው ከራሳቸው ድርጅታቸውን የሚያስቀደሙ ሊሆኑ ይገባል ማለት ነው።

ይህ ሳይሆን ሲቀር ሊጠየቁበት የሚያስችል ድርጅታዊ ስራት መዘርጋትና ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጁ ገለልተኛ አካላት ሊኖሩ ይገባል። መሪዎች የያዙት ሃላፊነት እና ቦታ የሚያደርስባቸውን ግፊትና ፈተና ተቋቁመው ከአድሎ ነጻ በመሆን በዙሪያቸው የተሰባሰቡትን የአባላት ስሜት ምን እንደሆነ ለመረዳትና ከአብዛኛው አባላት ስሜት አብሮ ለመሄድም ሆነ ስሜትን ለማስተካከል የተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል።

ይህንን መነሻ በማድረግ ግንቦት 7 የፍትኅ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በ2001 ዓ.ም. ሲመሰረት ካለፈው ስህተታቸው ተምረው ታግለው ያታግሉናል በሚል እምነት ከዚህ ቀደም በፖለቲካ ድርጅት ታቅፈው የነበሩም ይሁን ያልነበርን የትግሉን ጎራ የተቀላቀልነው፡፡ አለመታደል ሆኖ ግን ተስፋ የጣልንበት ድርጅት ከአራት ዓመታት በኋላ አህያ ቀንድ ቢያወጣ፤ ቂራ ቢነጣ የነበረ ማንነታችውን መለወጥና መማር በማይችሉ መሪዎቹ አምባገነንነት ውስጡ በነቀዘ እንደተበላ የብሳና ዛፍ ድርጅቱ አለን ስንለው እንደሌለ አድርገውታል፡፡

በግንቦት 7 አመራር ግን ይሄ ወሳኝ የሆነ የአመራር ብቃት ጎደሎ ብቻ ሳይሆን ሆን ተብሎ በአካባቢያቸው ከተሰባሰቡ ግለሰቦች ውጭ የሚመጣ ሃሳብን እንደ ጠላት የመቁጠር ብሎም ማናለብኝነት፤ ግብዝነትና አምባገነንነት ቁልጭ ብሎ ይታያል። ይሄም ብቻ ሳይሆን ድርጅቱ ሲመሰረት ጀምሮ ማድረግ የምንችለውን ማድረግ ከማንችለው ለይተው ማስቀምጥ አቅቷቸው አባላትንና ደጋፊዎችን በማይጨበጥ ሕልም አንዴ በ6 ወር ለውጥ እናመጣለን ሌላ ጊዜ የአረቡ ማዕበል ኢትዮጵያ ውስጥ ልናመጣ ነው የሚል ስሜታዊነትን የሚያጦዙ የማይጨበጥ ተስፋ በመስጠት ህዝቡን ሲያደናግሩ ኖረዋል።

Ginbot 7 Democratic

አባላት ለድርጅቱ ጥንካሬና ለልህቀት ብቃት ስንል ጊዜያችንን፤ ገንዘባችንን፤ ጉልበታችንና እውቀታችንን በተፈለገው ጊዜና ቦታ ሁሉ ሳንሳሳና ሳንለግም ከላይ ከተቀማጡና እንመራሃለን ከሚሉት ጥቂት ግለሰቦች የበለጠ መስዋዕትአድርገናል፡፡ አለመታደል ሆኖ እኛ ስንገነባ እነሱ እየናዱት ያለፉትን አራት ዓመታት ያለምንም ውጤት አባክነናል፡፡ በውጭ ሆኖ ለሚመለከተው ግንቦት 7 ትልቅና ውስብስብ ራሱን አገር ለመምራት የተዘጋጀ ድርጅት መስሎ ይታይ ይሆናል፡፡ እውነታው ግን ከዚህ በብዙ መልኩ የተለየ ነው፡፡

ለዚህም የምናነሳቸው ዋና ዋና  ነጥቦች፤

- ኤርትራን እንደ ብቸኛ የትጥቅ ትግል ማካሄጃ በማድረግ  ከአባላት ይሁንታ ሳያገኙ መጓዛቸውና ይህም ፍሬ እንደማያፈራ እየታወቀ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት  ያላግባብ ላለፉት አራት ዓመታት እንዲባክን መደረጉና ሆን ተብሎ አላስፈላጊ መስዋዕትነት መከፈሉ ፤ (በዚህ ጉዳይ ላይ ወደፊት ዝርዝር መግለጫ የምንሰጥበት ይሆናል)

- በአገር ውስጥ ምንም ዓይነት የትግል መረብ ሳይዘረጋ ከሶማሊያ ክልል ውጭ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች መሰረቶችን ዘርግተናል እየተባለ አባላት ማዘናጋትና አጉል ተስፋ እንዲኖራቸው ማድረግ፤

- ለስኬታማነታችን ወሳኝ የሆኑት የትግል አካሄዶች (በአገር ውስጥም ይሁን በትጥቅ ትግሉ ዘርፍ) በሁለት ውንድማማቾች እንዲያዙ መደረጉና ይህም ለተጠያቂት አስቸጋሪ ሁኔታን መፍጠሩ፤

- በድርጅቱ ውስጥ በቅንጅት ጊዜ ከነበሩት ከቀስተ ደመናና ከኤዲሊ አባላት ውጭ ሌሎች የድርጅቱ አባላት የሚሰጡት አስተያየት የማይሰተናገድበትና ጥያቄዎቻችው የማይመለሰበት እየሆነ መምጣቱ፤

- ጠቅላላ ጉባዔው በወሰነው መሰረት ድርጅቱ በየዓመቱ ምርጫ እንዲካሄድ ቢወስንም፤ ምርጫ ቢካሄድ የመሪነት ቦታውን እናጣለን ብለው በሰጉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትና ሙሉ ወርኃዊ ደመወዝ ከድርጅቱ በሚከፈላቸው ግለሰቦች ተጽዕኖ ምርጫ ሳይካሄድ ከአንድ ዓመት በላይ መቆየቱ፤

- የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ከየአገሩ ተመልምለው የሄዱ አባላትን የትጥቅ ትግል የለም ብሎ ማሰናበትና በሌላ በኩል ከነጭራሹ የሌለውን  የትጠቅ ትግል ያለ በማስመሰል አባላትንና ሌሎችን ማዘናጋት፤

- በጠቅላላ ጉባዔው የጸደቀውን የአባላት አደረጃጀትና መዋቅር ከላይ እስከታች ያለአግባብ በ7 የስራ አስጻሚ ኮሚቴ አባላት ውሳኔ ብቻ እንዲፈርስ መደረጉና ይህንን ህገ-ወጥ አካሄድ የተቃወሙ አባላት በየጊዜው በጉዳዩ ላይ እንድንወያይ ያቀረብነው ጥያቄ ተካይ ነቃይ ሹዋማና ሻሪ በሆኑ መሪዎች ውድቅ መደረጉና ጥያቄውን ይዘው የተነሱ አባላትን በወያኔነትና በአክራሪ አማራነት መፈረጅ፤

- በየጊዜው በውይይት መድረክ ላይ የተለየ ሀሳብ የሚያቀርቡ አባላትን ከአንድ መሪ በማይጠበቅ ጸያፍ ስድብና ዘለፋ ማዋረድና እነሱ ያሉት ብቻ ያለምንም ውይይትና ጥያቄ ተቀባይነት እንዲኖረው ማስገድድ፤

- ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጊዜያት በወገኖቻችን ላይ በደል ሲፈጸም ፈጥኖ መግላጫ ያወጣ የነበረው ድርጅት በደቡቡ የአገራችን ክፍሎች ሰፍረው ይኖሩ የነበሩ የአማራ ዝርያ ያላቸው ወገኖቻችን በመለስ ዜናዊ ወሳኝነት ከሰፈሩበትና ካለሙት መሬት ያለአግባብ እንዲባረሩ ሲወሰንና ታፍሮ ተከብሮ የኖረው ገዳማችን ዋልድባ በዶዘር ሲታረስ ግንቦት 7 ጉዳዩን አውግዞ መግላጫ እንዲያወጣ በዓለማቀፉ (የዲያስፖራ) ኮሚቴ በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብለትም ይህ የድሮ ስርዓትን ለማምጣት የሚፈልጉ ሰዎች ጥያቄ ነው በሚል ምንም

ዓይነት መግለጫ እንዳይወጣ ተደርጎ መቆየቱና በመጨረሻ ጊዜ ካለፈና ሁኔታዎች ሁሉ ከተረሱና የአባላትም ቅሬታ ገንፍሎ መውጣት ከጀመረ በኋላ አድርጌ ነበር ለማለት ብቻ የመግለጫ ቋንጣ ማውጣቱ፤

- የሙስሊም ወገኖቻችንን መሰረታዊ ጥያቄ ከበስተጀርባ በግንቦት 7 እንደሚመራ በማስመሰል የሚደረገውን የሙብት ትግል ጠልፎ ለራስ በማድረግ በሰው ሥርግ ለመዳር መሞከር፤
- ለራሷ ያልተነሳች ልታቋቁም ሄደች እንዲሉ የግንቦት 7 የአመራር አባላት የውስጥ ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ ሌሎችን እናስታርቃለን በሚል ዓመታትን የፈጁ ጊዜያት በከንቱ ማበከናቸው፤
- የስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ሰድባችኋል ተብለው ያላግባብ አባላት ሲባረሩ፤ አማራን ያህል ህዝብ በየጊዜው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሚሳደቡ እንደ አቶ ቸኮል ጌታሁን ዓነቶች ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ቢቀርቡም ርምጃ እንዳይወሰድባቸው መደረጉና እንዲያውም የምክር ቤት ሰብሳቢ ሆኖ እንዲሾም በመደረጉ ከምክር ቤቱ አባልነት ግለሰቦች በራሳቸው ፈቃድ ድርጅቱን ጥለው እንዲሄዱ መደረጉ፤ ይህ የአማራ ጥላቻ እንደ አቋም በሌሎች የስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ አባላትም መያዙ፤ይህም ግንቦት 7 ከያዘው መሰረታዊ አቋም በመውጣት የወያኔን ያህል በአማራ ላይ ዘመቻ እንዲዘመት መደረጉ፤
- ጥቂት ግለሰቦች ከጊዜ ወደጊዜ ድርጅቱን እንደ ግል ንብረትነት እየቆጠሩት መምጣታቸውና ድርጅቱ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ አንድም ጊዜ የስራ ግምገማና ኦዲት አለመደረጉ፤

በነዚህና በሌሎች ወደፊት እንደየአሰፈላጊነቱ በምንገልጻቸው ጉዳዮች ምክንያት ግንቦት 7 ዲሞክራቲክን ለመመስረት ተገደናል፡፡ መሠረታዊ መርኋችን የማይደፈርና የማይገሰስ የኢትዮጵያ አንድነት፤የሕዝብ እኩልነት፤የዲሞክራሲ ሙብቶች መጠበቅና የሕግ የበላይነት ናችው፡፡

ከሰላምታ ጋር

የግንቦት 7 ዲሞክራቲክ የጋራ አመራር

የኢትዮጵያ አንድነት ለዘላለም ይኑር!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ለምትሰጡን አስተያየት የኢሜል አድራሻችን፡ pr@ginbot7d.org ሲሆን

ድረ-ገጻችንን፡ www.ginbot7d.org

Ginbot 7 Democratic